የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
# የተሰጠ መግለጫ

ቀን ነሓሴ 3/2008 ዓ.ም

ለመላው ነጻነትና እኩልነት ናፋቂ የኢትዮጵያ ሕዝብ!

በሰላማዊ መንግድ የምትታገሉ የሲቪክ እና የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም የወያኔ ኢሃዴግ ሽብርተኛ ድርጅት በፈጠረው የጭቆና ግዞት አልበገር በማለት በሃገር ቤትና በዱር በገደሉ በነፍጥ በመዋደቅ ላይ ያላችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዓባላትና ደጋፊዎች።

በሀገራችን ኢትዮጵያ የጥፋት ማሕለቁን ጥሎ የሚገኘው የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ በፈጠረው የዘረኝነት፣የማህበራዊ አንድነት ፣የፍትህ ዕኩልነት እና የመናገር ነጻነትን በማፈን ዜጎችን እየገደለ፣እያሰረና እያፈነ ለስደትና ለሞት እየዳረገ ያለውን የወያኔ ኢሃዴግ ስረዓት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመጣል በሚደረገው ርብርብ የኢትዮጵያን የቁርጥ ቀን ልጆች ይዞ የተነሳው የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በጥር 2/2007 ከግንቦት 7 የፍትህ የዲሞክራሲና የነጻነት ንቅናቄ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ውህደት መፈጸሙ ይታወሳል።

"ጉድና ጅራት ከወደ ኋላ እንደተባለው" ሆነና በአሁኑ ወቅት ግንቦት 7 ሌላ ችግር ይዞ ብቅ አለ።

በኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አመለካከት ''አንድት ሃይል ነው'' በሚለው መሪ መፈክሩ ጠላትን በጋራ መግቢያ መውጫ በማሳጣት ህዝባችን የናፈቀውን የነጻነትና አብሮ የመኖርን ብሎም የዜጎችን ክቡር ህልውና ለመታደግ እንደሆነ ያምናል ይታመናልም ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
EPPF
ኢ.ሕ.አ.ግ.

ይሁን እንጂ ከውህደቱ ሂደት ማግስት ጀምሮ በአሰተናጋጅ ሃገር እና በውጪ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ከፍተኛ አመራር አካላት ጋር ተስማምቶ ከመስራት ይልቅ ልዩነቱ እየሰፋ አሁን ካለንበት ደረጃ ደርሰናል።

ለዚህም ከሚጠቀሱት ተጠቃሽ ዋና ጉዳዮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ቆራጥና ነባር ታጋዮችን ከድርጅቱ በማስወገድና ስም በመስጠት፣
- ከድርጅቱ የጋራ እውቅና ውጪ ከፍተኛ አመራሮች(ስራ አስፈጻሚ) ያልመከሩበት እና ያልወሰኑትን በአንባገነንነት ተደጋጋሚ ወሳኔዎችን በማሳለፍ
- የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ከፍተኛ አመራር(ስራ አስፈጻሚ) ዕውቅና ውጪ ከህውሃት /ኢሃዴግ ጋር ድርድር መጠየቅ እና አቁራጭ መንገድ መፈለግ።

- የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የስራ አስፈጻሚ አባላትን ባገለለ ሁኔታ ከሃገር ወዳድ ኢትዮጵያን አባላትና ደጋፊዎች በስማችን የተሰበሰውን ገንዘብ ምክክርና ውሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ ከድርጅቱ እምነትና ፍቃድ ውጪ ታዓማኒነትና ተጠያቂነት በሌለበት በከፍተኛ ወጪ በግልና በቡድን በመዳዝ ከፍተኛ የሆቴል፣የአበል . . ወዘተ ወጪዎችን በማውጣት።

- ገንዘብና ስልጣኑን ወርሃዊ ክፍያ ደሞዝን ለግንቦት 7 ጥቂት ተጠቃሽ ከፍተኛ አመራር በማድረግ <<መራራውን የህይወት መስዋዕትነትና የነጻነት ትግል ለአርበኛው በማድረግና ለዕለታዊ ጉርሱ ከደጋፊው ደጀኑ የተላከለት ገንዘብ ትራፊው እንኳን ሳይደርሰው በመቅረቱ።
- በውጪ የሚገኙ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር አመራሮችን በማስወገድና እስካሁን ድረስ ውህደቱን ባለመፈጸም በማን አለብኝነት የቡድን ድርጅታዊ እንቅስቃሴን በመቀጠል ወይም የመዋጥ ፣የማጥፋት እና አርበኞችን ከስማቸው ጭምር የመሰረዝ ስራዎችን በግንበት 7 ከፍተኛ አመራሮች ማሰራቱ።

- መሪ ሆነው የተቀመጡት ፕሮፌሰር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ አመራሮችንና አጋር ድርጅት መሪዎችን ባግባቡ ከማነጋገር ይልቅ በመሳደብና በማሸማቀቅ እንዲሁም ያለድርጅቱ ዕውቅና ከስራ ቦታቸው ለረዥም ጊዜያት በጋራ ውሳኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች በመተው መሰወር በተለያዩ ጊዚያት ከግንባር እንዳሉ ሆነው በተደጋጋሚ የሃሰት ፕሮፖጋንዳ በመንዛት "ላም በሌለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ" ህዝባችንን በማሳሳት ራስን ሃገር ወዳድና ጀግና አድርጎ በማቅረብ።

በተለያዩ ጊዜያቶች ህዝብን የውሸት ተስፋ በመስጠትና በማዘናጋት ያልተደረጉ የትግልና የውጊያ እንቅስቃሴዎችን እንደተደረጉ አድርጎ በማቅረብ "ለምሳሌ" ፊሽካው ተነፋ በሚል የአምስት ቀን ውጊያ ተደርጓል ፣ በቅርብ ጊዜ ደግሞ በአርባምንጭ አማሮ ተደረገ የተባለው (የአካባቢው ገበሬዎች በግብርና ማዳበሪያ ዕዳ ምክናየት የተከሰተ ህዝባዊ ግጭትን) የድርጅቱ እንቅስቃሴ አድርጎ በማቅረብ።

- ለፖለቲካ ፍጆታ በሚል በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ በሃገር ወስጥ ያሉ የተቃዋሚ ድርጅት አባሎችን ለወያኔ ክስ አመቼ የሆነ የድምጽና የጽሁፍ ማሰርጃ በሚድያ የአርበኞች ግንቦት 7ን ቀላቅሎ የፕሮፖጋንዳ ስራ በመስራት የወያኔ ሰለባ ሆነው በየእስር ቤቱ እንዲሰቃዩ ምክናየት በመሆን!!
- በተናጠል ግንቦት 7 ብቻውን ያለ አንዳች ውይይትና ምክክር የአርበኛውን ከፍተኛ አመራር ያላሳተፈ ወህደት ወይም በጋራ ለመስራት በሚል ፈሊጥ ''ሃገራችን ገብተን እንሰራለ'' ከሚል የኦሮሞ ዲሞክራት ኮንግረስ ከእነ አቶ ሌንጮ ለታ ጋር በግንባሩ ስም የማይታወቅ ድርድር ማድረግ!! የውህደቱ ሂደት በተለያዩ ሃገራት ያለመሳካት ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው።

ይህ ችግር ስር ሰዶ ለዚህ ደረጃ ከመብቃቱ በፊት በተለያዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚው በፈቀደው ስብሰባ እና ግላዊ ግንኙነቶች ሊለወጡ የሚገባቸው ዋና ጉዳዮች በአርበኛው በኩል መፍትሄ ሃሳብ ቀርቦ አፈጻጸሙ ወጤት አልባ ሆኗል።

ይህን ሁሉ ችግር ከጅምሩ ይዞ ይንቀሳቀስ የነበረው የአርበኞች ግንቦት 7 ድርጅት ሁኔታዎቹ እንዲለወጡ የገንዘብ መሰብሰቢያ ባንኩ በጋራ እንዲሆን ቢጠየቁ ከአፍ እሺታ ባለፈ ፈቃደኛ ያለመሆንና ግልጸኝነት መጓደል፣በውጪ ሃገር እንደ ቀድሟቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር አባላትን ሳይጨምር በአብዛኛው ሃገራት ግንቦት 7 ብቻቸውን በመሰባሰብ በየቦታው በተናጠል መሰባሰቡን ቀጥለዋል። በጣም የሚገርመው በተጠራው የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት (fundraising event ) ላይ በሚደረገው ውይይት እንኳን "አርበኞች ግንቦት 7" የሚለውን ስም ከመጠቀም ይልቅ " ግንቦት 7 " እየተባለ ወይይቱ የቀጠሉበት ሁኔታዎች በርካታ ናቸው !!

በውጪ የሚገኙ ተቃዋሚ ኢትዮጵያውያን ላይ ስልጣናቸውን እየቀያየሩና የድርጅቱን ገንዘብ በደሞዝ ፣በአበል፣በራንስፖርት . . ወዘተ ወደ ኪሳቸው በማስገባት በዲያስፖራው ያሉትን prominent የሆኑ ግለሰቦችን ያለ ጉባኤው ወሳኔ ከድርጅቱ እንዲወጡ መደረጉ ሊጠቀስ የሚገባው ነው።ይህን በተመለከተ አግባብ ያለው ስራ ያለመሆኑ እናም መታረም እዳለበት ቢነጋራቸውም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ለውይይትም ሆነ በጉዳዩ በቂ መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ አልሆኑም።

ከዛም በላይ በመግለጫው ሊካተቱ የማይችሉ ወታደራዊ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦትንና ወታደራዊ ጥያቄዎችን ችላ ከማለት ባለፈ እጅግ በጣም የዘገዩ ምናልባትም ለድል ሊያቃርቡን የሚችሉ ኩነቶች ላይ በማላገጥ የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራሮችና የድርጅቱ መሪዎች ትግሉ እንዳይራመድ አግደውት ወይም ለትግሉ ጋሬጣ ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል በቅርቡ በአማራ ክልል በሰሜን አርማጭሆና ወልቃይት ጠገዴ ህዝባዊ ትግሉን ችላ ማለት ከሚጠቀሱት አንዱ ነው።

ከላይ በዝርዝር የቀረቡና ከውህደቱ ማግስት ጀምሮ ጠላትን ላለማስደሰት ሲባል ውስጣዊ ማስተካከያ እንዲደረግ በተደጋጋሚ ወይይት ተደርጎ በግንቦት 7 ከፍተኛ አመራርና ግላዊ አመለካከት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል።

በተጨማሪም ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በዲያስፖራውና በየስብሰባው የሚያውሩትና ድርጊታቸው ፍጹም ከተግባሩ በተቃርኖ ሆኑ ሰላገኘነው, እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ

አርበኞች ግንባር የቀድሞ አመራር አባላት ከደጋፊዎቻችን ጋር በመሆን አፋጣኝ እና ጊዜ የማይሰጠውን የትጥቅ ትግል ለማድረግ ከዛሬ ነሃሴ 3/2008 ጀምሮ ውህደቱን ያቋረጥን እና የግንቦት 7 አመራሮች ፕሮፌሰር ዶክተር ብርሃኑን ጨምሮ ያሰናበትን መሆኑን በአንክሮ እንገልጻለን። በማስከተል የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር አባላትና ደጋፊዎች እንደቀድሟችሁ በየሃገራቱ ቻፕተሮቻችንን እንድታጠናክሩ እና ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዓለም አቀፍ ኮሚቴ በኩል የሚወጡ መመሪያዎችንና የሃገር ወስጥ ትግል ስትራቴጂን እንድትከተሉ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር